Beide-Mariam Ejigu
Feb 2014

# መጽሐፈ ጉባኤ ዘ፴ወ፬ መጻሕፍተ
# ልሣነ ግእዝ እለ ኢተዐልዋ
# ኀበካልእ ልሣን

በአማርኛ ካልተተረጐሙና በሕትመት ላይ ካልዋሉ 34 የግእዝ መጻሕፍት ተጨምቆ የተዘጋጀና የመጻሕፍቱን ይዘትንና ምንነትን የሚያስረዳ መልካም ግንዛቤንም የሚያስጨብጥ መንፈሳዊና ሥጋዊ መጽሐፍ

አዘጋጅ ገብረዩሐንስ ገብረማርያም

www.ethiopianorthodox.org

2003 ዓ.ም

መጥፋት ያመለክታል ሌላም ተመሣሣይ ችግር አለ ግእዛቸውና ራብአቸው ባንድ ድምፅ የሚነገሩ ፊደሎች አሉ እነሱም ሀ፣ሃ፣ሐ፣ሓ፣አ፣ኣ፣ዐ፣ዓ ናቸው::

እነዚሁ ሁሉ የጥናት ሣይሆን የልምድ ስያሜ ተሠጥቶአቸዋል:: ከንባብም ሆነ ከሥነ ጽሑፍ እንኳንስ የተግባር የሐሳብም ተሞክሮ የሌላቸው ሁሉ ለምን ሆሄያትን አትጠብቅም እያሉ የዘለፋ ናዳ ያወርዱብኛል የነሱን አልከባይነት ፍሬ አልባ ነው::

ስለ ግእዝ ጥናት ከተነሳ ስለቅኔም መታሰቡ የማይቀር ነው ቅኔ የሚለው ቃል ብዙ ትርጉም አለው:: በግእዝ አካሄድ የሚሠጠው ዋናው ትርጉም ግን ምሥጋና ነው አሁን «ቅኔ» የምንለው በ15ኛውና በ16ኛው ክፍለ ዘመን በአማራሳይንት ዙሪያ እንደተጀመረ ይነገራል:: አባባሉ ግን በጥናት የተመረከዘ ሳይሆን አፈ ታሪክ ነው:: በስፋት እንደተነገረ የምንረዳው በዘመነ ጎንደር ነው::

እንደሚታወቀው በጎንደር ያላንዳች ሥራ የታጨቁ ደብተሮች በተዋህዶ የባህርይ ልጅ፣ በቅብአት የባሕርይ ልጅ የሚል ብሂል አመነጩ ይህ ለቤተ ክርስቲያን መጥፎ አካሄድን አመጣ ሦስተኛም ክርስቶስ በሰውነቱ የፀጋ ልጅ ነው አይደለም የሚል አጨቃጫቂ መንገድ ተፈጠረ::

ለዚሁ የርስ በርስ መጎሻሸም የተጠቀሙበት ቅኔን ነው:: ቅኔ የዋርካ፣ የጎጃም፣ (በጎጃም የጎንጅና የዋሸራ) የሚል ስምም ወጣለት:: ቅኔን የተማረ ብዙ ምሥጢር ግልፅ ይሆንለታል፣ በተለይ ለግእዝ ቋንቋ ዋና መሠረቱ ቅኔ ነው እተባለ በየአቅጣጫው ይተረካል ይደሰኮራል:: በዘመናችን ቅጥ ባጣ ጩኸትና መወራጨት በቅኔ ስም ምንም ፍሬ የሌለው፣ የግእዝን ቋንቋ አካሄድ ያልጠበቀ የቅኔ ቅርፅ ይሰማል:: የባለ ቅኔው ወዝየለሽ ያለቅጥ መጮኽ የሰሙ ቢጤዎቹ ምንም ያዳመጡት ፍሬ ነገር ሳይኖራቸው በጭብጨባ፣ በፉጨትና በጩኸት ድጋፋቸውን ያስተጋቡለታል::

ቅኔ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዐይነተኛ የድክመት ምንጭ ሆኖ ነው የኖረው በግእዝም ይሁን በየብሄሩ ቋንቋ ወንጌል ለክርስቲያን ምዕመናን እንዳይነገር ምዕመናን ከአምልኮተ እግዚአብሔርና ከትምህርተ ድሂን ርቀው የአምልኮተ ባእድ ሰለባዎች እንዲሆኑ ሰው ሠራሽ ቅኔ በሩን ዘግቶባቸው ኑሯል::

በቅኔ ምክንያት ብዙዎች ለውሸት ሲዳረጉ ኑረዋል ምንም ሣያስቡና ሳያሰላስሉ ከመቅፅበት ቅኔውን እንደሚያጎርፉት ይናገራሉ:: በቅኔ ውስጥ የዜማ መጠን አለ፣ ንኡስ ደቂቅና ዐቢይ አገባብ አለ፣ ገቢር ተግብሮ አለ፣ ወዳቂና ተነሺ ዐቢይ ዐንቀፅ ንኡስ አንቀፅ አለ ... ይህን ያቀፈ ሞያ በቅፅበታዊ ሰዓት አቀርባለሁ ማለት ፍፁም ውሸት ነው ግን ይህ ውሸት ከመቼ ጀምሮ እንደተለመደ ባይታወቅም ባሁኑ ጊዜ ብሶበት ይታያል:: ከዚህም በተጨማሪ የቅኔ መምህር ነኝ ባይ እጅግ በዝቷል የዚህም መለኪያ እንደታረደ በሬ ማጓራት ብቻ ነው:: ያሬዳዊ ማህሌትን ለማዳመጥ ብሎ ቅኔ ማሕሌት የሚገባ ሁሉ በነዚህ የቅኔ መምህራን ነኝ ባዮች ልቅ ጩኸት እጅግ ይበሳጫል ያፍራል በቅኔ ስም አታላይነትና አስመሳይነት ተቆራኝተውት ያለምንም ውጤት ዕድሜውን የገፋ ሕዝብ ሥፍር ቁጥር የለውም የመጽሐፍ መምህር ነኝ ባይም እንዲሁ::

ይህ መጽሐፍ በግእዝ ከተጻፉ 34 የብራና መጻሕፍት ተውጣጥቶና በአማርኛ ተዘጋጅቶ ቀርቧል ዝግጅቱ የተውጣጣባቸው ሠላሳ አራቱ መጻሕፍት ለአንባብያን በቀላሉ የማይገኙ ናቸው:: ቢገኙም ለብዙ ኢትዮጵያውያን የግእዝ ቋንቋ እንግዳ ስለሆነ መጻሕፍቱን አንብበው የሚረዱት የተወሰኑ ሰዎች ናቸው:: በሌላ በኩል ችሎታ እያለው ከመጻሕፍቱ ጋር ለመተዋወቅ የፈለገ ሁሉ ከላይ እንደተገለፀው መጻሕፍቱን አግኝቶ ለመመልከት ውጣ ውረዱ ብዙ ነው የመጻሕፍቱን ይዘት ለመጠቆም ያህል ይህ አነስተኛ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል::

## ክፍል ፩

### ፊስአልጎስ

ፊስአልጎስ ማለት የፈላስፋ ስም ነው:: ይህ ፊስአልጎስ የተባለው ፈላስፋ የጻፈው መጽሐፍ በአምስተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በስድስተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ገደማ ከተለያዩ የሮም ግዛቶች እንደመጡ የሚነገርላቸው ዘጠኙ ቅዱሳን እንዳመጡት ብዙ ታሪክ ምሁራን ዘግበዋል:: ይህ ፈላስፋ የክርስቶስን በዚህ ዓለም መመላለስና የቅዱሳት መጻሕፍትን ምሥጢር ከአራዊትና ከአእዋፍ ጋር በምሳሌነት እየገለፀ ያስተምራል:: መፅሐፉ በአምሳ ሰባት ክፍል የተከፈለ ነው::

ይህ ፈላስፋ ምሳሌያዊና መንፈሳዊ ትምህርቱን ዮሐንስ ወንጌላዊ በራእዩ በአንበሳ መስሎ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን መነሻ ያደርጋል:: ቃሉም የኸውና እነሆ ከዳዊት ሥር የሆነ ከይሁዳ ወገን አንበሳ መጣ ከአብ ዘንድም ተላከ በጅራቱ ዓየር "ተሸፈነ" ይልና ጅራቱ ያለው ምልክቱ ነው እንደ መላእክት ሁኖ በሥልጣንም ሁኖ በሰው ሥርዓት ሰው ሁኖ ተገለፀ........

ይህ አባባል ትርጉምን ያስተምረናል አንበሳ ሲተኛ ዐይኑን ይገልፃል ሲነቃ ዐይኑን ይሸፍናል የተኛም ይመስላል ክርስቶስ መለኮታዊ ሥልጣን እያለው 3 ቀንና 3 ሌሊት በመቃብር ተኛ ስለዚህም ሰሎሞን እኔ የተኛሁ ነኝ ልቤ ግን የነቃች ናት ያለው ስለ ክርስቶስ ሞት ነው ዳዊት እስራኤልን የሚጠብቀው ፍፁም አይተኛም አለ:: ሦስተኛው ምሳሌ አንበሳም ምውት ግልገልን ከወለደች ወንዱ አንበሳ እስኪመጣ ድረስ ትጠብቀዋለች:: ወንዱ አንበሳ በ3ኛው ቀን መጥቶ ሦስት ጊዜ ሲተነፍስበት የሞተው የግልገል አንበሳ ይነሳል:: ይህም የክርስቶስን በ3ኛው ቀን መነሳትን ያመለክታል:: እግዚአብሔር አብ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሞት አስነሳው:: አፈክራድዮን ስለተባለውና በኦሪት ዘዳግም ስለተመዘገበው ፊሲአልጎስ እንዲህ ይላል ይህ ወፍ ነጭ ነው:: ምንም የጥቁርም ሆነ የሌላ መልክ በጠጉሩ የለም ሁለመናው ነጭ ነው:: ይህ ወፍ በነገሥታት ቤት ነው የሚገኘው:: በጠና ደዌ የተያዘ ሰው ቢኖር ዓይኖቹም የታወረ ካለ የታመመው ሰው የሚሞት ከሆነ ይህ ወፍ አያየውም የማይሞት

www.ethiopianorthodox.org

## መቃብያን

መቃቢስ የሚባል የሜዶን ሰው ነበር። ለሱም ሦስት ልጆች ነበሩት ስማቸው አብያ፣ሲላና፣ ፎንቶስ ይባላሉ። ባገራቸው ዓመፀኛ ንጉሥ ስለተነሳ ሕዝብ ሁሉ ለጣኦት ላለመስገድ ወሰኑ። በዚሁም በንጉሡ ብዙ የሥጋ መከራ ደረሰባቸው። ንጉሡ በግቢው ቀለብተኞች የሆኑ አንበሶች እንዲበሉባቸው ሰደደባቸው አንበሶቹ ግን እነሱን ትተው ወደሱ ፊናታቸውን አዞሩ ንጉሡ ሸሽቶ አመለጠ።

በዚሁ አጋጣሚ ሌሎች ወንድሞቻቸው ደርሰው ከእሥር ፈቱዋቸውና ሸሽተን እናመልጥ ቢሉዋቸው ከሰማዕትነት አንሸሽም አሉ። ንጉሡም በበኩሉ በነሱ ፅናት እንደተመለሰና እግዚአብሔርን እንዳመነ ክፍል አንድ ይገልፃል።

ሁለተኛው ክፍል ኤዶማዊው መቃቢስ ከመሶፈጣምያና ከሶርያ ጀምሮ እስከ ትውልድ አገራቸው ድረስ በነበሩ አይሁድ ላይ ተነስቶ ሞአባውያንንና ሜዶናውያንን በማስተባበር እንዳስጨነቃቸው ይገልፃል። ኢየሩሳሌምንም እሱ አጥፍቷታል። የመቃቢስ አገር በሞአብ ውስጥ የምትገኝ ሬማት ትባላለች። ይህ ሰው በኢየሩሳሌም ላይ ብዙ ጥፋትን አድርሷል።

ሦስተኛው ሰብለኔዎስ በመባል የሚጠቀስ ርኩስ መንፈስ ነው። ይህ ርኩስ መንፈስ የሰውን ልጆች ከእግዚአብሄር መንገድ ለማራቅ ብዙ እንደቀባጠረ መፅሐፉ ይገልፃል።

በአራተኛው ክፍል የተጻፈው ግን ራእየ ዳንኤል ነው። ዳንኤል ይህን ራእይ በምርኮ ባቢሎን ጊዜ እንዳየው ይታወቃል። ዳንኤል ከሠልስቱ ደቂቅ ጋር በባእድ አገር እግዚአብሔርን ያመለከ የንጉሥም ሕልም የፈታ የእግዚአብሔር ነቢይ ነው።

መጽሐፈ መቃብያንም ቀዳማዊ ካልእና ሣልስ በመባል በኢትዮጵያ መፅሐፍ ቅዱስ ሠፍሯል።

## ትምህርተ ሐዋርያት /ገድለ ሐዋርያት/

ይህ መጽሐፍ የቀሌሚንጦስ ዘሮም ራእይ የቅዱስ ጳውሎስ ገድልና ትምህርት የሌሎች አሥራሁለት ሐዋርያት ትምህርትና ገድል ይዟል። በስተመጨረሻው የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሐረገ ትውልድ ከአሥራሁለቱ ነገደ እራኤል ውስጥ እንደሆነ ያስረዳል።

መፅሐፉን የተረጎመው አባ ዲዮናስዮስ ሲሆን የምሥራቅ ሰው መሆኑን ይገልፃል። ከምን ቋንቋ እንደተረጎመው ግን አልተገለፀም። የዚሁ መፅሐፍ ፀሐፊ አይታወቅም። ከሰባ አርድእት ውስጥ አብሮኮሮስ ሉቃስና ቀሌሚንጦስ ብቻ በጸሐፊነት ተጠቅሰዋል።

## ገድለ ሰማዕታት

ከኔሮን ቄሣር ዘመነ መንግሥት /64 ዓ.ም/ ጀምሮ በተከታታይ ለሁለት ተኩል ክፍለ ዘመናት በክርስቲያኖች ላይ ብዙ ግፍ ተፈጽሟል። የነሱ ደም በከንቱ አልፈሰሰም ቤተክርቲያን በፅኑ መሠረት ላይ እንደትቆም አድርጓል።

ዘመነ ሰማዕታት በቤተክርስቲያን ካላንደር ትልቅ ሥፍራ አለው። ቤተክርስቲያን ዘመነ ሰማዕታትን ራሱ የቻለ የዘመን አቆጣጠር እንዲኖር አደረገች። በዚሁም መሠረት ዓመተ ሰማዕታት ራሱ የቻለ የዘመን አቆጣጠር እንዲኖረው አድርጋለች። በዚሁም መሠረት ዓመተ ሰማዕታት የሚል ካላንደር/የዘመን መቁጠሪያ/አላት።

የሰማዕትነት መንገዶች ሦስት ናቸው። እነሱም መገደል፣ አገር ጥሎ መሸሽና መታሰር ናቸው። ይህ መፅሐፍ የሃያ አራት ሰማዕታትን የሰማዕትነት ታሪክ ይዟል። ከነዚህ ውስጥ አሥራ አንዱ ሴቶች ናቸው። የሰማዕትነታቸው ታሪክም በትምህርትሠጭነቱ እጅግ ከፍተኛ ነው።

ለመንፈሳዊ ዓላማቸው ሲሉ ለሰበሱት ሥጋ ቅንጣት ያህል ሳይሳሱ ክርስቲያኖች በመሆናቸው ቤተክርስቲያን በዓለም ደምቃ እንድትታይ አድርጓል። ከዚህ መጽሐፍ ማንኛውም ሰው ሊያገኝ የሚችለው ትምህርት በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ሰው በቀላሉ የሚቸነፈውና ለብስጭት የሚዳረገውዓላማቢስ ስለሆነ ነው። ዘለዓለማዊ ሆነ ጊዜያዊ ጥቅም አልጋ በአልጋ ሆኖ ለማግኘት አይቻልም።

www.ethiopianorthodox.org

## ሥንክሳር

ሥንክሳር /ሳናሕሪ/ ከሚለው የውጭ ቋንቋ የመጣ ስያሜ ነው ትርጓሜው ስብስብ ማለት ነው። ሥንክሣር የጻድቃን የሰማዕታት የሐዋርያት የነቢያትና የመላዕክት ታሪክ ባጭር ባጭሩ ይገልጻል የኢትዮጵ ስንክሳር ከመስከረም እስከ መጋቢት ከመጋቢት እስከ መስከረም ድረስ በሁለት የተከፈ ነው።

የመስከረሙ ሥከሣር የግብፅና የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር አንድ ነው ይላል መስከረም 1 በዚሁ ዕለት ኢዮብ ጻድቅ በርተሎሚዎስ ሐዋርያ ራጉኤል መልአክ እንደሚታሰቡ ይገልጻል። የሌሎችም መስተጋድልን አበው ታራ በዚሁ ተዘግቧል። መጥምቁ ዮሐንስን ግን አልመዘገበውም እሱን መስከረም 2 ብቻ ነው የመዘገበው።

ይህ ሥንክሣር የተጻፈበት ዘመን አልተመዘገበም ሥንክሳር የተባለው መጽሐፍ በ903 ዓመተ ሰማዕታት ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተሰበሰበ ራሱ መጽሐፉ ይናገራል። ከመጀመሪያው ስብስብ የመሲግ ኤጲስቆጶስ አባ ሚካኤል እና የቦሩልስ ኤጲስቆጶስ ዮሐንስ ከሌሎች መምህራነ ቤተክርስቲያን ጋር በመሆን እንደቀዱት በመፅሐፉ ከመጀመሪያው ዐምድ ላይ ተመዝግቧል።

ከመጋቢት 1 ቀን የሚጀምረው ሁለተኛው ክፍል በወርሐ መጋቢት የቀንና የሌሊት ርዝመት አንድ እንደሆነ ይገልጽልናል። ከዚህ ቀጥሎ በዕለቱ የመዘገበው በርኩሰስ የተባው የኢየሩሳሌም ጳጳስን ነው። ሥንክሳር ዕለትን እንጂ ዓመተ ምሕረትን አይመዘገብም። ስለዚህ ታሪካቸው በዚሁ መጽሐፍ የሠፈረው ሁሉ የነበሩበትን ዘመን ለማወቅ አይቻልም።

ጳጉሜን ስድስት ሲሆን በዚሁ ዕለት ታሪኩ የተመዘገበለት ማንም የለም ግን በዚሁ ቀን የሚነበብ አጠቃላይ ምዕዳን አስቀምጧል። በካላንደር /የዘመን አቆጣጠር / ደግሞ ሮባ ግብፅና ኢትዮጵያ አንድ እንደነበሩ መዝግቧል።ይህ መጋቢት እስከ መስከረም የሚነበበው ሥንክሣር ወልደ ሩፋኤል የተባለ ሰው እንደገለበጠው /እንዳጻፈው/ብቻ መዝግቦአል የተጻፈበት ዘመን ግን አልመዘገበም።

## መጽሐፈ በረላም

ይህን መጽሐፍ ከህንድ ተገኝቶ ወደ ቤተ መቅደስ ወደ ኢየሩሳሌም እንደመጣና የጌቴሴማኒ ሰው የሆነ መነኩሴ አባ ዮሐንስ ደግሞ እንደጻፈው በስተመግቢያው የሠፈረው ጽሑፍ ይነገረናል። ወደ ትሩፋት የምትወስድ መንገድ ወጣ ገባና አባጣ ጎርባጣ የበዛባት እግዚአብሔርን ለሚያምኑ እጅግ ወደ ላይ የመጠቀች ናት በማለት ይመክራል።

"ወዳጎሉ" የሚባል ዮናናዊ ንጉሥ ነበር። ይህ ንጉሥ በገዳማውያን መነኮሳት ላይ ብዙ ግፍ ፈፀመ። በኋላም አንድ ወንድ ልጅ ብቻ ወለደ። ይህንንም ልጅ የዋሰፍ ብሎ ሰየመው። ይህ ዮናናዊ ንጉሥ ሕንድን ይገዛ ነበር። የዋሰፍንም በሕንድ ነው የወለደው። የዋሰፍ የሕንድ የፋርስንና የሌሎችም የሩቅ ምሥራቅ አገሮች ጥበብን እየተማረ አደገ።

ይህ የዋሰፍ የተባው ሕጻን አባቱ ከሰው እንዳይገናኝ ያደረገበትን ምሥጢር ለመረዳት ፈለገ። ግን ምክንያቱ ለመየጠቅ የፈለገው ለተመደበለት ሞግዚት ብቻ ነበር። በዚህ ጊዜ እኔ በእስር እንድኖር እንደልቤ ወድያ ወዲህ እንዳልል ከሰዎች ተለይቼ እሥረኛ ሁኜ ዕድሜዬን እንድገፋ የተፈረደብኝ ምክንያቱ ምንድን ነው? በማለት የሚወደውን ሞግዚት ጠየቀ።

ሞግዚቱም አባቱ መሢሐውያን ክርስቲያንን በማሳደድ የታወቀ መሆኑን ከገለጸለት በኋላ እኛም የክርስቲያኖቹን መከራም ሆነ ስለዚህም ዓለም ከንቱነትን እንዳንገልጽልህ አጥብቆ አዘዘን። ይህን ምሥጢር ግን በልብህ ያዘው...... ሲል ገለፀለት። ከዚችው ዕለት ጀምሮ የዋሰፍ ይህን ሞግዚት በአባትነት ደረጃ ተመለከተው።

ከዕለታት አንድ ቀን አባቱን /ንጉሡን/አባቴ ሆይ ዕረፍት የነሣኝ አንድ ነገር አለ እኔን ከሰው ሠውረህ የምታስረኝ ለምንድን ነው? አለው። አባቱም /ንጉሡ/ ይህን ያደረግሁበት ምክንያት ከክፉ ርቀህ አሳዛኝ ነገርን እንዳታይ ብዬ ነው። በደስታ ብቻ እንድትኖር ስለፈለግሁ ይህን አደረግሁ አለው።

የዋሰፍ አንተ አለ የተባው መልካም መብልና መጠጥ እያቀረቡልኝ



www.ethiopianorthodox.org

በኢጲስቆጶስ እጅ ተጠመቀ፣ አንቢየር የዋሰፍን በሥጋ ወለደው የዋሰፍ ደግሞ አባቱን አንቢየርን በመንፈስ ቅዱስ ወለደው፣ በሌሎች ዐላውያን ነገሥታት ተሰደው በየጫካው የተደበቁት ሁሉ ወደሱ ተሰበሰቡ።

አንቢየር ንጉሥ ትምህርተ ክርስትናን ሲረዳ በሥልጣን ዘመኑ ያፈሠሠውን የሰው ደም እጅግ እንገበገበው ጠቅላላ መንግሥቱን ለልጁ አስረክቦ በምናና ተወሰነ፣ በልቅሶና በሐዘንም እግዚአብሔርን ለመነ፣ ይህን የተባረከውን ልጅ በማግኘቱ እጅግ ደስ አለው። እየመላለሰ ልጁን የዋሰፍን ይስመው ነበር።

አንቢየር በልጁ ቤት ሆኖ ጥቂት ጊዜ ተቀመጠ። ከዚህ ዓለምም በሞት ተለየ፣ ልጁም የዋሰፍ በክብር እያለቀሰና መንፈስዊ ደስታ እየተሰማው በምሥጋና፣በዝማሬ ቀበረው። በመቃብሩ ላይ እየተገኘም ምሕረትን ከእግዚአብሔር ይለምንለት ነበር።

የዋሰፍ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እኔ ንጉሥነቱን ትቼ አምላኬን ልከተል ስለ ወሰንኩ መሪያቹን ምረጡ አላቸው /ለሕዝቦቹ/። እነሱ ንግ የሱን መሪነት በማጣታቸው አዘኑ፣ እነሱም ካንተ በቀር ሌላ መሪ የለንም በማለት እጅግ ታወኩ። ከብዙ ውጣውረድ ብኋላ በራስያስ ንጉሥ ይሁንላችሁ አላቸው። ይህ በራስያስ የአንቢየር ታማኝ መኮንን የነበረና በኋላም ከየዋሰፍ ጋር በሥልጣን የሠራ ነው።

በራስያስ ከልቡ እምነት የገባው ሆኖ ስለነበር እኔም ንጉሥነትን አልፈልግም፣ባለንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር እያነበብክ እንዴት አንተ ይህን ከባድ ሸክም በኔ ላይ ለመጫን ትመክራለህ? አለው። የዋሰፍም ከበራስያስ ተቃውሞ ሲሰማ ግድ ማለቱን አቁሞ ደብዳቤም ጽፎ "ከበራስያስ በቀር ሌላውን አታንግሡ" ብሎ ትቶ በሌሊት ጠፍቶ ሄደ። ሕዝቡ መጥፋቱን ሲሰሙ አለቀሱ። ሊፈልጉትም ተሯሯጡ፣ ግን ሊያገኙት አልቻሉም። ከጊዜ በኋላ ግን እጆቹን ዘርግቶ እየጸለየ ካንድ ወንዝ አጠገብ አገኙት።

እሱም በከንቱ አትድከሙ ካሁን ወዲያ እኔ ንጉሥ አይደለሁም አላቸው፣ ግን ብዙ አዝነው አለቀሱበት ወደ ቤተመንግሥት ተመለሰና ሕዝቡን ድጋሚ ንጉሥ እንደማይሆን ገለጸላቸው። እስከ ቻለ ድረስ ተልእኮውን እንደፈጸመም ገጸላቸው እያለቀሱ መሄጃ ባሳጡት ጊዜም በራሱያስን ለእናንተ ሹሜዋለሁ አላቸው። በራሱያስ ደግሞ እኔ አልችልም ንጉስ ሁኜ የመምራት ችሎታ የለኝም አለ።

ሕዝቦቹ ግን በራስያስን በግድ አነገሡት የዋሰፍም ስርዓተ መንግሥትን ፈጸመለት። እግዚአብሔር በእምነት ይጠብቀው ዘንድም ጸለየለት በትክክል ሕዝቦችን እንዲመራ አደራ አለው፣ ብዙ ትምህርትም ከቅዱሳት መጻሕፍት እየዘረዘረ አስተማረው። ሕዝቡም በፍቅርና በሰላም እንዲመሩ አደራ አላቸው በያሉበትም ለእግዚአብሔርም እንዲገዙ መከራቸው። በራስያስና ሕዝቡም የሱ የየዋሰፍ መለየት የነሱ ሞት እንደሆነ ገለጹለት፣ እጅግም አለቀሱ ከእግዚአብሔር ጋር ያስተዋውቃቸው እሱ እንደሆነ እየተናገረ አንተ ንጉሣችን ብቻ አይደለህም፣ የሃይማኖት አባታችንም ነህ አሉት።

ትቷቸው ለመሄድ ሲንቀሳቀስ እያለቀሱ ተከተሉት፣ እጅግ በመረረ ሁኔታም ተለያቸው መምህሩ በረላም የሰጠው ጨርቅ ነበረው በዘመነ መንግስቱ በውስጥ የለበሣት ነበር። በመጨረሻ ግን እሷን ብቻ ለብሶ መነነ። በጉዞው ጊዜ መሸቶበት ካንድ ድሃ ቤት ደረሰና መቀየሪያ ትሆነው ዘንድ የያዛትን ልብስ ሰጠው። የመምህሩ በረላምንም ፊት ያሳየው ዘንድ እግዚአብሔርን ለመነው፣ ሰበአዊ ጠባዮችንም አቸነፋቸው።

በገዳም በምናኔ ሥጋውን አቸነፋት፣ አስቃያትም ቅጠላቅጠልም እየተመገበ ሕይወቱን መራ። ጸላኤሰናዮት ቀድመውን የንጉስነት ክብሩን በማሳየት ብዙ ተፈታተነው በሐብት በምድራዊ ምቾት በክብር...ወዘተ ተፈታተነው ሁለት ዓመት ሙሉ በበርሃ ቆይቶ መምህሩ በረላምን አገኘው። ሁለቱም ተቃቀፉ፣ተሳሳሙ፣እጅግም ተከባበሩ። ከሚጠፋው ዓለም ወደማጠይፋው ዓለም በአካለ ሥጋ ሊሸጋገር በመቻሉ ተደሰተ።ከተለያዩ ጀምሮ የደረሰበትንም ሁሉ ይዘረዝርለት ዘንድ በረላም ጠየቀው። እሱም የደረሰበትን ሁሉ ገለጸለት።

www.ethiopianorthodox.org

በዋሻው አጠገብ በረላም እየኮተኮተ ለምግብ ከማያሳድጋቸው ቅጠሎችም ተመገቡ፡፡ ካጠገቡ ካለው የውሃ ምንጭም ጠጡ፡፡ ሁለቱ አጠገብ ላጠገብ ሁነው ተጋደሉ ይህንንም አለም አቸነፉት፡፡ በመጨረሻም በረላም ከዚህ ዓለም እንደሚለይ በራዕይ እንደተገጸለት የዋሰፍም እንዲበረታ ብዙ ምዐዳን ሰጠው፡፡

የዋሰፍ በዚህ እኔም ውድቀት እንዳያገኘኝ ስለምፈራ እረፍተ ነፍስ ካንተ ጋር አገኝ ዘንድ ወደ ፈጣሪ አማልደኝ በማለት ብዙ አለቀሰ፡፡ አረጋዊው በረላም ግን ልጄ ሆይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ትቃወም ዘንድ አይገባህም በጽሞና ልትታገስ ይገባል፡፡ እድሜዬ ወደ መቶ አመት ተጠግቶዋል፡፡ በዚህ ምድረ በዳ መኖር ከጀመርኩ ደግሞ 75 ዓመቴ ነው፡፡ ስለዚህ አንተ በዚህ ገድል ብዙም ሳትቆይ ትችላለህ ይህ የእግዚአብሔር ውሳኔ ብቻ ነው አለው፡፡ የዋሰፍ ከበረላም ትምህርተ ክርስትና ከተሰጠው በኋላ 25 ዓመት ቆይቶ ነው ብህትውና የጀመረው በበሕትውና ደግሞ 75 ዓመት ኖረ በዚሁ ብህትውና እያለ ብዙዎችን ወደ አሚነ ክርስትና አምጥተዋል፡፡

በረላም ሲሞትም የዋሰፍ በክብር ገንዞ ቀበረው፡፡ የዋሰፍ ሲሞት ደግሞ ያ የዋሰፍ በረላምን ለመፈለግ በጉዞ ላይ እያለ በእንግድነት የተቀበለው ደግ ሰው በክብር ገንዞ ቀበረው፡፡ በዓመተ ሰማዕታትም በ1233 ዐረፈ፡፡

ይህ መጽሐፍ ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ በአጼ ገላውዲዎስ ትዕዛዝ ተገልብጦ ያለቀው ሕዳር ሲሆን በ7040 ዓመተ ኩነኔ ነው የተጻፈው ከዓረብኛ ወደ ግእዝ የተረጎመው እንባቆም ይባላል፡፡ ይኸውም በንጉሱ ገላውዲዎስ ታዞ ነው፡፡ እንደገና ከግዕዝ ወደ ግዕዝ በ1958 ዓ.ም ተገለበጠ፡፡

እንባቆም የተባለው አባት ትውልዱ የመን ሲሆን ከኢትዮጵያ ወደ የመን በባርነት ተሸጠው በተወሰዱት ኢትዮጵያውያን ባልና ሚስት አማካይነት ከእስልምና ወደ ክርስትና የገባ ሰው ነው፡፡ እነዚህ ባልና ሚስት በይፋትና ጥሙጋ ክርስቲያንና በአዳሎች መካከል ይካሄድ የነበረው ጦርነት አማካይነት ተማርከው ለዓረቦች የተሸጡ ነበሩ፡፡ ባልዩው የመርሃ ቤቴ ተወላጅ ሲሆን ሚስቱ ደግሞ የትግራይ ተወላጅ ነበረች፡፡

እንባቆም ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በዘመነ እስክንድር እንደሆነ



የታሪክ መጻሐፍት ያረጋግጣሉ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ በኋላ ከደብረ ሊባኖስ ዕጨጌነቱም በነገስሪዎች ሁለት ጊዜ ተባሯል፡፡ ዕጨጌ እንባቆም መፅሐፈ ቄደርን ጨምሮ የተለያዩ መጻሕፍትን ዕፏል፡፡ በተለይም በግራኝ ወረራ ጊዜ ዓረብኛን በመቻሉ ብዙዎችን ከሞት ታድጓል፡፡

## የገዳመሲሀት መነኮስ አባ ሙሴና የሌሎቹም መነኮሳት ራዕይና ታሪክ

ገዳመሲሀት ግብፅ ውስጥ እንደሚገኝ ከተለያዩ የብራና መጻሕፍት ማስረጃ እናገኛለን፡፡ ከብህትውናም ብዛት የየወሩ መባቻ ብቻ እንጂ የአመታትና የወሮች ስያሜ ተረስቶ ነበር /በገዳሙ መናንያን ዘንድ/፡፡ አውሬዎቹ ከአባ ሙሴ ጋር መልካም ጉርብትና መስርተው ነበር፡፡

የሙሴ ዘሲሀትን ታሪክ የጻፈ ሳሙኤል ይባላል፡፡ የጻፈውም በዮናናውናን ቋንቋ ነው፡፡ ይህ ሳሙኤል የሙሴ ዘገዳመሲሃትን ታሪክ ጽፎ አልዋሃት ወደተባለው ቦታ ተመላላሾች ነጋዴዎች ከሆኑ ለአንዱ ሰጥቶታል፡፡ ለነጋዴው በአደራነት ጽፎ የሰጠውንም በእስክንድርያ በሚገኘው የቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን እንዲያኖረው ነው፡፡

## አባ ብንያሚን

አባ ብንያሚን የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳሰት ሲሆን ከኢትዮጵያ ኖባ ሌላ ሶስት አህጉረ ስብከቶች ነበሩት፡፡ ከዚህ ተያይዞ ገድላቸውና አለተ-እረፍታቸው የተጻፈው ገዳማውያን መነኮሳት ናቸው፡፡

## መፅሐፈ ስነ ፍጥረት

መፅሐፈ አክሲማሮስ እያሉ ብዘዎች በቃል ይናገሩታል፡፡ ነገር ግን የመጀመሪያው ክፍል የያዘው አምስቱ አዕማደምሥጢር ሲሆን በሁለተኛው ክፍል ደግሞ መርሐዕውር ይገኛል፡፡ በሦስተኛው ክፍል ሥነፍጥረት ይገኛል፡፡ በስተመጨረሻም ክፍል የቅዳሴ ማርያም አንድምታ ትርጉምን እናገኛለን፡፡ መፅሐፉ የቆየ ነው መቼ እንደተፃፈ ግን አይታወቅም፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ስለጣና ከእመቤታችን ስደት ጋር የተያያዘው አባባል ከራእየ ማርያም የተወሰደ ነው።

በየምዕራፉ በእገሌ ቀን የሚነበብ ድርሳን የሚል ፅሑፍ ሠፍሮበታል አንደኛው ምዕራፍ ዜና ፅንሠታ፣ ሁለተኛው ምዕራፍ ገብርኤል ስላበሠራት የሚገልፅ ድርሳን የኪዳነ ምህረት ድርሳን የአስተርእዮ ድርሳን የልደት ድርሳን የፍልሰታ ድርሳን በመባል የተዘገቡ አሉ።

የአስተርእዮ ድርሳን የተባው እመቤታችን ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየች በኋላ የተፈፀሙ ምሥጢራትን ለመግለፅ የተደረሰ ነው እንጂ በድጓውና በሥርዓተ ማሕሌት እንደተመዘገበው አይደለም። ድርሳን ተብሎ በስተ መጨረሻው የሠፈረው ፅሑፍ ጢሞቴዎስ ዘእስክርድርያ ከፃፈው ከነገረማርያም የተወሰደ ይመስላል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በትንቢተ ዘካርያስ ምዕራፍ አንድ ቁጥር ሰባት ላይ የሚገኘውን /ሣባጥ/ የሚለው ቃል የወርሐ የካቲት ስያሜ ነው /አይደለም/፣ የመጋቢት መባቻ ነው በመባባል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ካህናት ሲከራከሩበት ይሰማል። ይህ ቃል /ሳባጥ የሚለው/ በዚሁ መፅሐፍ ይገኛል። የካቲት አሥራ ስድስትን ለመጥቀስ አመ ፲ወ፮ ለወርሐ ሣባጥ ዘውእቱ የካቲት ተብሎ ተዘግቧል። ሣባጥ ቢልና ሣቤጥ ቢል የአፃጻፍ ጉዳይ እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም።

ያዕቆብ ሐዋርያ /የጌታችን ወንድም/ የእመቤታችን ዜና እንደጻፈው ይህ መፅሐፍ ይናገራል። እንደፅሑፉ አገላለፅ ያዕቆብ በአይሁድ እጅ ከተገደለ በኋላ ይህ ፅሑፍ ሲገኝ ችሏል።

## ክፍል ሁለት ገድለ ስማዕታት

ፊቂጦር ዘአንፆኪያ፡- ፊቂጦር የቤተክርስቲያንን መጻሕፍት የመረመረ ሊቅ ነበር የምሥራቅ ንጉሥ የልጅ ልጅም ነበር። ግን አባቱም ሆነ አያቱ አረማውያን ነበሩ አያቱ የክርስቲያንን ደም በማፍሰሱ የሚታወቀው ዲዮቅልጥያኖስ ነው።



ከዲዮቅልጥያኖስ ሚስቶች አንዷ መካን ስለበረች በቅንአት ፊቅጦርን ልትገድለው ትፈልግ ነበር። አንድ ቀን ልቀፊው ብላ ወስዳ ከደረጃ ላይ ወረወረችው ግን በእግዚአብሔር ኃይል ሊድን ችሏል ። እናቱ /ማርታ/ በቤተክርስቲያን ትምህርት ቤት አስገብታ አሳደገችው።

አያቱ ዲዮቅልጥያኖስ ቤተክርስቲያንን ለመዝጋት ሲነሳ ማርታ ብዙ ጭንቀት እየደረሰባት ትደብቀው ነበር። ሕርማኖስ የተባለው የፊቂጦር አባት ከክርስትና ወጣ /ዲዮቅልጥያኖስን ለማስደሰት/፣ ማርታ የዲዮቅልጥያኖስ ልጅ ናት።እሷም ከልጇ ጋር የክርስቶስ ተከታይ በመሆን ፀናች። ፊቅጦር በአያቱ በዲዮቅለጥያኖስ ብዙ የስጋ መከራን ተቀብሏል እናቱ የድዮቅልጥያኖስ ልጅ ማርታ ግን መከራውን እንዲታገሥ እንጂ በመከራ ዕናትና ብዛት ወደ ክህደት እንዳይመለስ ታበረታታው ነበር። እሱም ብዙ የሥጋ መከራን ታግሦ ቆይቶ በመጨረሻ በሰይፍ አንገቱ ተቆርጦ ሰማዕትነትን ተቀበለ። ሰማዕትነትን የተቀበለው ሚያዝያ 27 ቀን ነው።

<u>ዮሐንስ ዘስንሑት</u> ፡- የዮሐንስ ዘስንሑት ሥራ የበግ እረኝነት ነበር ። የዲዮቅልጥያኖስ አረማዊነትን ሲያውቅ ወደ መንፈሳዊ ተጋድሎ ገባ። ተጋድሎን የጀመረው አትሪብ በምትባል አገር ነው። በዚችው አገር ድምፅን ከፍ አድርጎ ስመክርስቶስን ሲጠራና ክርስቲያንነቱን ሲገልፅ የአህዛብ መኮንን አፉን ለጎመው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ብዙ የሥጋ መከራዎች ደርሰውበታል። ግንቦት ስምንት ቀን ሰማዕትነትን ተቀበለ።

ጰርሶቆስና ኬልቄዶን በተባሉ ክፍሎች የክርስቲያን ማሕበር ነበር። ከማህበረ ክርስቲያን ውስጥ አፎምያ አንዷ ናት። አፎምያ የሁለቱን ክፍሎች ክርስቲያኖች መሪ ሆነች። መሪነቷ መከራን በመታገሥና ከዲዮቅልጥያኖስ ከሐዲ ትእዛዝ በመውጣት ነው፣ አፎምያን ጨምሮ በኬልቄዶንና በጰርሶቆስ በሚገኙ ክርስቲያኖች ላይ ብዙ መከራ ደርሷል።

ከመከራው ክብደት ክርስቲያኖቹ ወደኋላ እንዳይሉ ቅድስት አፎምያ ግንባር ቀደም ሁና የሚደርስባትን የሥጋ መከራ በእኩቴት ተቀበለችው። ገናናዎቹን የዲያቅልጥያኖስ መኮንኖች አቸንፋ በኬልቄዶን በሰማዕትነት አረፈች

www.ethiopianorthodox.org

ኡራልያኖስ ቄሣር በንጉሥነት እያለ ሁለት ዓመት ሙሉ ዝናብ ቀረ ክርስቲያኖችም አሳዷል። ከዝናብ ማጣት የተነሳ ረሀብ ፀና ንጉሡና ቤተሰቡም በረሀብ ሊያልቁ ሆነ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን እንዲለምኑ ተማፀናቸው። በነሱ ጸሎትም ዝናብ ዘነበ ረሀብም ቀረ። ካራቱ ወንጌሎች መካከል የሉቃስን ወንጌል ብቻ የሚቀበል መርቅያን በዘመኑ ተነሳ። በዘመኑ ጳጳሳት ተሰባስበው የዐበትቱን ቁጥር አወጡ።

ቴውዳስ የተባለው ቄሣር በነገሠ ጊዜ ጋሊኖስ የተባለ ፈላስፋ ተነሣ የሕክምና ሞያም ነበረው ብዙ መፃሕፍትንም ተርጉሟል። ቄሣር ቴውዳስ የሱ /የጋሊኖስ/ አብሮአደግ ስለነበር ሰው በመግደላቸው ሞት የፈረደባቸውን ሰዎች እንዲሠጠውና አካላታቸውን እየቀደደ እንዲመራመርባቸው ቄሣሩን ጠየቀው ቄሣሩም ፈቅዶለት በሰዎች አካል ይመራመር ነበር።

በቄሣር ቴውዳስ ዘመነ መንግሥት ዩልዮስ የተባለው ሊቀጳጳስ በእስክንድርያ ተሾመ ከእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አሥረኛው ነው በዘመኑ ዲሜጥሮስ ተነሣ። ያለጊዜው ያፈራ ወይንንም አግኝቶ ዲሜጥሮስ ለሊቀጳጳሳቱ ወሰደለት። ሊቀ ጳጳሳቱ ዩልዮስም ዲሜጥሮስ ከሱ ቀጥሎ ሊቀጳጳሳት እንደሚሆን ትንቢት ተናገረለት።

መክሲሞስ ቄሣር ክርስቲያንን ከሳደዱ የሮም ቄሣሮች አንዱ ነው "ታኦላ" የተባለውን የአንፆኪያ ሊቀጳጳሳት ገደለው። መርክዮስ የተባለው የኢየሩሳም ሊቀጳጳሳት በሽሽት በቄሣሩ ከመገደል አመለጠ።

በእሥክንድር ዘመን አቆጣጠር አምስት መቶ አርባ አምስት የፋርሱ ንጉሥ ስቡር ወልደአዝዱር ከነገሠ በሃያ ሦስተኛው ዓመት እለእስክንድሮስ ቄሣር ነገሠ። በዚሁ ንጉሥ ዘመን ክርስቲያኖች ዕረፍት አግኝተው ነበር። እሱ ከነገሠ በሰባተኛው ዓመት ያሮክላስ ሊቀጳጳሳት ሁኖ በእስክንድርያ ተሾመ እሱ ከግብፅ ጳጳሳት 13ኛው ነው።

ጎርጎርዮስ ገባሬተአምር በእሥክንድር የዘመን አቆጣጠር 551 ተነሳ ጎርጎርዮ በቂሣርያ ነበረ በዘመኑ የነበረው የሮም ቄሣር ንርድያኖስ ሲሆን በፋርስ ደግሞ ብሀራም ማኒን ገደለውና ተከታዮቹ ተሰደዱ ሁለት መቶ ያህሉ ከማኒ ተከታዮች ግን በንጉሡ ተገድዋል በዚሁ ዘመን አብቃኖስ የተባለው ፀሐፊ ተነሳ። የዘመናት ሂደትና ያለፉትን ነገሥታት ታሪክ እንዲሁም በየአገሩ የተከሰቱ መጥፎዎች ሆኑ መልካሞች በዚህ ዕሑፍ ሰፍሯል።

አባ እንጦንስ የመነኮሳት አባት ፊሊጶስ ቄሣር በነገሠ ጊዜ ተነሳ ፊሊጶስ



ቄሣር ለክስቲያኖች ዕረፍትን የሠጠ ነበር የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ 14ኛው ሊቀጳሳት ዲዮናስዮስም በዚሁ ዘመን ነበር። እምነትም ይሁን ክህደት በሕሊና ብቻ ይወሰናሉ በቃል ቢክድ /ቢያምን/ ክህዷ /አማኒ/ አይባልም የሚሉ በዚሁ ዘመን ተነሱ ተከታይም ግን አላገኙም።

ከዘመነ እስክንድር አቆጣጠር 569 ዓመት ቄሣር ሉርያኖስ ነገሠ። በክርስቲያኖች ላይም ከባድ ስደትን አደረሰ። ዱሚያኖስና ቆዝሞስ በሱ ሰማዕትነትን ተቀበሉ። የኢየሩሳሌሙ ሊቀጳጳሳት እለእስክድሮስ በሱ ሰማዕትነትን ተቀበለ ዱሚያንስና ቆዝሞስ ወንድማማች ሲሆኑ እናታቸውም አብራ ሰማዕትነትን ተቀብላለች የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ መክሲሞስ 15ኛው በሱ ዘመን ተሾመ ሉርያኖስ ልጁን ፋርስን እንዲቆጣጠር ወደዚያ ላከው ነገር ግን ብሕራም የተባለው የፋርስ ንጉሥ አሸነፈው አንገቱንም ቆረጠው ቄሣር ሉርያኖስ የልጁን መገደል ሲሰማ እጅግ አዘኖ በክርስቲያኖች ላይ የሚፈፅመውንም ግፍ አቆመ።

ገላድዮስ ቄሣር በእስክንድር ዘመን አቆጣጠር 579 ዓመት ነገሠ። በዘመኑ የእሳት አክሊል ቅርፅ ያላቸው አራት ከዋክብት ታዩ። በዚሁ ዘመን ጳውሎስ የሚባል በአንፆኪያ ላይ ሊቀጳጳስ ሆነና ክርስቶስ መለኮታዊ አይደለም በእግዚአብሔር ለሰው ልጆች ድሕነት ብቻ ተመረጠ አለ ከዚሁ ስሕተቱ ሳይመለስም ሞተ የሱንም የስሕተት ሃይማኖት ብዙዎች ተቀበሉ።

ጳውሎስ በሥልጣን ላይ ስምንት ዓመት ቆይቶ ሲሞት አሥራ ሦስት ሊቃነጳጳሳት በአንፆኪያ ተሰብስበው ትምህርቱንና ተከታዮቹን አወገዙ።

ታኦና የእስክንድርያ 17ኛው ሊቀጳጳሳት ሆነ በሱ የሕይወት ታሪክ የሚቀጥለው ተገኝቷል። ኡልያኖስ ቄሣር የክስቲያኖችን ጠላት ስለነበር የእስክንድርያ ምዕመናን በድብቅ ሥርዓተ አምልኮትን ይፈጽሙ ነበር። ይህ ሊቀጳጳሳት ክርስቲያኖችን እንዳያሳድዱበት መደለያ ገንዘብ ይሠጣቸው ነበር። እንዲህ እያለ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ቤተክርስቲያን ሠራ ቤተክርስቲያኑ ተሠርቶ ሲያልቅ ክርስቲያኖች በዚሁ በግልፅ መፀለይ ጀመሩ። ከታኦና ቀጥሎ አርዮስ ቄሣር ነገሠ ክፉ ከሐዲ ነበር ከነሱ በስተመጨረሻ በእስክንድር አቆጣጠር 505 ዓመት. ዓለም ከተፈጠረ በአምስት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና ሰባት ዓመት ዲዮቅልጥያኖስ ተነሳ። ዲዮቅልጥያኖስ በመጀመርያ የፍየል እረኛ ሁኖ ሲዘፍን ፍየሎች ከሱ ጋር ይዘፍኑ ነበር ጥሩ ድምፅ ነበረው ወደቤተመንግሥቱም የገባው ዘፈን በመቻሉ ነው። ጥሩ ዘፋኝ መሆን የንጉሡን



www.ethiopianorthodox.org

ምልክት እንቀሳቀሳት::

ኖህ ከመርከብ በሚያዝያ ወጣ ኖህ ሊሞት ማንም ተመልሶ ወደ መርከቢ እንዳይገባ አዘዘው:: ሴም በበኩሉ የአዳምን ሥጋ ይዞ ከፋሌት ልጅ መልከፄዴቅ ጋር ወደጎልጎታ ለመሄድ ሲነሳ ከሱ በኋላ ማንም ሰው ወደ መርከቢ እንዳይገባ አስጠንቀቃቸው ሴም መልከፄዴቅን አባቱን ፋሌትንና እናቱን አስፈቅ፦ ነው ከሱ ጋር እንዲሄድ ያደረገ::

ሴም የአዳም ሥጋ በጎልጎታ አስቀምጦ ሲመለስ ዩሴዴቅ የተባለውና የመልከፄዴቅ አባት ፋሌት ወደሱ መጡና መልከፄዴቅን የት አደረስከው አሉት በዚህ ጊዜ ሴም በመንገድ ታሞ ሞተ እኔም ቀበርኩት አላቸው:: ፋሌት ከሴም ቀጥሎ በአምስተኛ ትውልድ ላይ የሚገኘው ኤቦር ልጅ ነው:: ኖህ በሕይወቱ እስከ ስድስተኛ ትውልድ የልጅ ልጅ አይቷል:: የኤቦር የልጅ ልጅ የፋሌት ልጅ መልከፄዴቅ በሰባተኛ ትውልድ ተወልዶ ለአካለ መጠን ደርሶ ነበር::

ራግውም የፋሌት ልጅ የመልከፄዴቅ ወንድም ነው:: መፅሐፍ ቅዱስ ናምሩድ የኩሽ ልጅ እንደሆነ ይናገራል ኃይለኛ የመጀመሪያ ንጉሥ እንደሆነም ይገልፃል የነገሠበትን አገር ግን አይገልፅም ቀሌሚንጦስ መጀመሪያ በባቢሎን ቀጥሎ መላ ዓለምን ናምሩድ እንደገዛ ይገልፃል::

በራዕዩ ናምሩድ ዘውድ በሰማይ አየሁ ብሎ እሱ እንዳየው አድርጎ ሱሱን የተባለው አንጠረኛ እንዲሠራለት አዘዘው እሱም ሠራለት በሱም የነገሥታት ዘውድ መድፋት ተጀመረ:: ቀሌሚንጦስ ለዘውዱ አጀማመር አስመልክቶ "ወበእንቲአሁ ይቤ ዘአልቦ አእምሮ ከመወረደሎቱ አክሊል እምሰማይ" /አእምሮ የጎደላቸው ሰዎች ለናምሩድ ከሰማይ ዘውድ እንደወረደለት ይናገራሉ/ ብሏል::

ከናምሩድ ቀጥሎ ሴሩኅ ከሴሩኅ ቀጥሎ ፍርቆር ከፍርቆር ቀጥሎ ናኮቶል ነገሠ:: ሰባ በተባለው ከተማም ግንብ ሠራ:: ሰባ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሴቶች የነገሱባት ናት የሴቶቹ መንግሥት እስከ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ቀጠለ/ይህ ሱባ ሰባ የምንለው ነው/::

ከናምሩድ ቀጥሎ በነገሠው ሴሩኅ ዘመን ሰዎች እግዚአብሔርን በመተው ጣዖትን ማምለክ ጀመሩ:: እግዚአብሔርን ማምለክን ተው መጽሐፍ ቅዱስ ፋሌት ራግውን ብቻ እንደወለደ እንጂ መልከፄዴቅን እደወለደ አይገልፅም

ሴሩህ ናኮርና ታራን እንደወለደ በመግለፅ ቀሌሚንጦና መፅሐፍ ቅዱስ አንድ ናቸው ቀሌሚንጦስ በታራ ዘመን የተፈጸመውን ታሪክ እንደሚከተለው

ያስቀምጣል:: በዘመኑ አንድ ሀብታም ሰው ሞቶና የሀብታሙ ልጅ የአባቱን ምስል በወርቅ አስቀርፆ በመቃብሩ ላይ አኖረ:: ይህ ልማድ በማንም ሰው ተለምዶ ነበርና ልጁ ምሥሉ እንዳይሠረቅ ጠባቂ አስቀመጠለት ሠይጣን በምስሉ ላይ አድሮ ጠባቂውን በተቀበረው ሰው አንደበት ያነጋግረው ጀመር::

በዚሁ ጊዜ ሌቦች የልጁን ቤት ዘረፉ ልጁም ባባቱ መቃብር ላይ ሄዶ አለቀሰ:: ሠይጣኑም በተቀበረው አባቱ አንደበት ልጂ ሆይ አታልቅስ ልጅህ አምጠተህ እረድልኝና ገንዘብህን እመልስልህለሁ አለው እሱም ልጁን አምጥቶ አረደ:: ይህ ባህል በሁሉ ተለመደ ሰዎች ልጆቻቸውን ለጣዖት ለመሠዋት ይሽቀዳደሙ ጀመር::

መፅሐፍ ቅዱስ ሎጥን የአብርሃም የወንድም ልጅ ይለዋል ቀሌሚንጦስ ደግሞ የእህቱ ልጅ ይለዋል:: ሴም መልከፄዴቅን የአዳምን ሥጋ እንዲጠብቅ ሲመድበው ጥፍሩን እንዳይቆርጥ ጠጉሩን እንዳይላጭና እንስሳትን እዳይሰዋ መስዋእቱ ከንፁሕ ስንዴ ብቻ እንዲያደርግ እንዳዘዘው ይገልፅና ከአብርሃም ጋር በተገናኘ ጊዜ እግዚአብር ጥፍሩን እንዲቆርጥ ራሱንም እዲላጭ አዘዘው ይላል/ቀሌሚንጦስ/::

አብርሃም ወደ ፈርኦን ገብቶ በነበረ ጊዜ ፈርኦን ለሣራ አጋርን አገልጋይዋ ትሆን ዘንድ ሠጣት ይስሐቅ ሊሰዋ ሲቀርብ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ነበር፡ ሊሠዋበት የነበረው ቦታ ደብረማኖስ ይባላል:: ጌታችን በዚሁ ቦታ ነው የተሠቀለው አዳምና ሄዋን በዚሁ ተፈጠሩ አብርሃም ከሰማይ የወረደውን በግ በዚህ አየ ይላል /ቀሌሚንጦስ/::

የመልከፄዴቅ ቅድስና አብርሃም ይስሐቅን ለመሥዋእት ካቀረበ ጀምሮ ታወቀ የኢየሩሳሌምንም መቆርቆር ተጀመረ:: የአለም ነገሥታት ከመልከፄዴቅ የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል መጡ እየተባረኩም ይሄዱ ነበር:: እያንዳንዳቸውም ከነሱ ጋር እንዲሄድ ለመኑት እሱ ግን /መልከፄዴቅ/ እግዚአብሔር ከዚያ እንዳይወጣ እንዳዘዘው ነገራቸው እነዚህ ነገሥት ተማክሩና ኢየሩሳሌምን በገንዘባቸው አንፀው በሷ ላይ እንዲሾሙት ተስማሙ መቅደስንም ሠሩለትና መቅደሷን ኢየሩሳሌም ብሎ ሰየማት ነገሥታቱም የነገሥታት አባት አሉት::

አንዳንድ ሰዎች መልከፄዴቅ አልሞተም ይላሉ ለዚህም መነሻቸው እንደመልከጼዴቅ የአለም ካህን አንተ ነህ የሚለው ነው ነገር ግን ዳዊት አይሞትም አላለም ሥጋ ለባሽ ፍጡር በመሆኑ ይሞታል:: ሙሴ የመልከጼዴቅን



www.ethiopianorthodox.org

በሀያ አራተኛው ዓንቀፅ ውስጥ ቁጥር ስድሳ አምስት ከንቱ ውዳሴ ከክርስቶስ ፍቅር ይለያል ብዙ አይሁዳውያን የኢየሱስ ክርስቶስ ድንቅ ተአምራት እያዩ የሱ ተከታዮች ለመሆን እጅግ ይጓጉ ነበር። ነገር ግን በካህናት አለቆች እንዳይናቁና ከነሱ የሚሰጣቸው ከንቱ ውዳሴ እንዳይቀርባቸው ከእምነት ወደ ኋላ አሉ እምነቱን የደበቀ ሰው ለብዙዎች መሰናክል ሊሆን ይችላል የማለት ምክር ያስተላልፋል።

በዓንቀፅ ሠላሳ አንድ ውስጥ ማንኛውን እንስሳ አርዶ የሚበላ ሰውን ከገደለ አይለይም የሚሉ ነበሩ ይላል። በዓንቀፅ ሠላሳ ከቁጥር ሁለት ጀምሮ አመክንዮ የተባለውና የሐዋርያት የእምነት መግለጫ የተሰኘው ይገኛል።

የዓንቀፁ መነሻ ቅዱሳት ሐዋርያት ስለተቀደሰችው የአምላክ አንድነትና ሦስትነት የሠጡት ትምህርት ይህ ነው። እኛም የእግዚአብሔር ልጆች ይህን የተቀደሰውን ቃል በትክክል ለሚታዘዙ ወገኖች እናስተላልፋለን በማለት ይጀምራል። አመክንዮ በቅዳሴ ውስጥም ሠፍሯል ከየተኛው መፅሐፍ እንደሚገኝ የተገነዘቡ ምናልባት ጥቂቶች ናቸው። ይህም ሊሆን የቻለው ይህ ዲዲስቅልያ የተባለው መፅሐፍ የሚገኝባቸው አድባራትም ሆኑ ገዳማት ጥቂቶች በመሆናቸው ነው።

ዐንቀፅ ሠላሳ አንድ፦ ከሚሞን መሠርይ መነሣት ጊዜ ጀምሮ ሠይጣን በቤተክርስቲያን እንዴት መለያየትን እንዳመጣ የሚገልፅ ሲሆን ብዙ መናፍቃን የተለያየ የመናፍቅነትን መንገድ አፍልቀዋል። ብዙ አማልክት አሉ ጋብቻ አያስፈልግም የሚሉና ሌሎችም በዘመኑ እንደተነሱ ይህ ዐንቀፅ ሠላሳ አንድ ይዘረዝራል። በቤተክስቲያን ታሪክ እነዚህ መናፍቃን ግኖስቲኮች በማለት ይገለፃሉ። ዋናው መነሻቸው በዕውቀትና በመመራመር ወደ እግዚአብሔር ክብር ይደረሳል የሚል ሁኖ የፍልስፍና አካሄዳቸው የተመሳቀለ ውጥንቅጡ የወጣና መሥመሩ ይህ ነው ለማለት የሚያስቸግር እንደሆነ የፍልስፍና ሊቃውንት ይናገራሉ።

የእግዚአብሔር አንድነትንና ሦስትነትን የሚገልፁ ቅዱሳት መፃሕፍትን በመመልከት ሦስት አማልክት አሉ የሚሉ ከነሱ መካከል ነበሩ ለነሱ መልስ አምላክ ሁለት አይደለም ሦስትም አይደለም ብቻው ለዘለዓለም የሚኖር እርሱ ነው እንጂ ተብሎ ተፅፏል። ከግኖስቲኮች መካከል ሁነው ሌላ ቡድን በማደራጀት ጋብቻን በመቃወም ለተሰለፉት ጋብቻ ንፁሕ እንደሆነ ለሚወለዱትም ልደት ርኩሰት እንደሌለበት እንናገራለን ሕዝቡ ይበዙ ዘንድእግዚአብሔር አዳምንና



ሔዋንን ብዙ ተባዙ ብሎ ፈጥሮአቸዋልና የሚለው መልስ ተሠጣቸው።

ባጠቃላይ ይህ አመክንዮ በመባል የሚታወቀው የሃይማኖት መግለጫ በውስጡ አጠቃልሎ የያዛቸው መልሶች በሃያ አምስት ቁጥር ተዘርዝረው ለብዙ መናፍቃን የተሠጡ ናቸው። ይህን አመክንዮ ካስቀመጠ በኋላ መፅሐፈ ዲዲስቅልያ እነዚህ ወንበዴዎች ናቸው እንደበጎች እየተመሰሉ ከእግዚአብሔር.... ጋር ይጣላሉ መሢሕ ክርስቶስን ሐዋርያትንና ነቢያትን ሐሰተኞች የሚያደርጉ አሕዛብንም በመጥፎ ትምህርታቸው የሚያስቱ ናቸው ራሳቸውን ደፍተውና ወደ ምድር አቀርቅረው በከፋታቸው የወይኑን ቦታ የሚያጠፉ ናቸው ብሎአቸዋል።

ቅዱስ ጴጥሮስ በነዚህ መናፍቃን ምክንያት ሐዋርያት ተሰብስበው ይህን መፅሐፈ ዲዲስቅልያ እንደፃፉ የገለፀበት ሐተታ ብዙ ነው። በሰላሳ ስድስተኛው ዐንቀፅ የመላእክት ምሥጋና /ቅኔ/ የሚል ይገኛል በሰዓታት ከሉሙ በማለት የሚጀምር የተለያየ የምሥጋና ዓይነት አለ። ይህ ከዚህ ላይ የሠፈረው ከሉሙ በምዕራፍ ውስጥ ይገኛል። በምዕራፍነቱም ለትምህርት ይቀርባል ይህ ዐንቀፅ የያዘውም ይኸው ብቻ ነው።

በሰላሳ ሰባተኛው ዐንቀፅ እለተ እሁድን እንዴት ማክበር እንዳለብን ይገልፃል እሁድ ሰንበትና እለተ ትንሣኤ በማለት ይጠቅሳታል። በዚችው ዕለት በየሣምንቱ ቀኑን ሙሉ የክርስቶስን ሕማማተ መስቀል እያስታወስን የትንሣኤው ፀጋ የምንሳተፍበትን ምሥጢር ለመረዳት እንድንችል ያስገነዝበናል አልፎ አልፎም እሁድ ሰንበት እያለ ዕለቱን ይጠቅሳታል የሚጸለየውንም ጸሎት /በእለተ እሁድ ሰንበት/ አስቀምጧል።

ከአህዛብ መካከል ለመጠመቅ የሚመጡት የሚሠጠው ትምህርት በሰላሳ ስምተኛው ዐንቀፅ ተቀምጧል። ከመጠመቃቸው ፀፊት ለተወሰነ ጊዜ ንኡስ ክርስቲያን እየተባሉ እንደሚቆዩም ይገልፃል። 39ኛው ለጥምቀት በቀረበው ውሃ ላይ የሚፀለይ ዐንቀፅ አርባ በሜሮን ላይ የሚፀለይና ሌሎችም አሉ መፅሐፉ አርባ ሁለት ዐንቀጾች አሉት።

ይህ ዲዲስቅልያተብሎ በመሠየም የቤተክስቲያንን ሥርዓት ያጠቃለለው መጽሐፍበሐዋርያትተዘጋጅቶበቀሌሚንጦስ፣በበርናባስ፣በጢሞቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በቲቶ፣ በሉቃስ፣ በአሶን፣ በሉኪዮስሱሲ በተባለው ጴጥሮስ እጅ ለምእመናን እንደተላከ በማጠቃለያው ተገልጿል።



www.ethiopianorthodox.org

በግብረ ሕማማት ከዚህ እየተመረጡ ብዙ ምንባቦች ተወስደው ገብተዋል በፍትሐነገሥትም የዚህ መፅሐፍ ዋና ዋና ነጥቦች ሠፍረዋል። መፅሐፉ በትሕትመት ላይ ውሎ ለሕዝበ ክርስቲያን እንዲዳረስ ቢደረግ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።



www.ethiopianorthodox.org